የሰበር መ/ቁ/255052

ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሠናይት አድነው

አመልካቾች፤ 1.አቶ ዮሀንስ ይማም 2. ወ/ሮ አስረስ ወርቅነህ ቀረቡ

3. አቶ ዮናስ ፍቃዱ 4. አቶ ሙልዬ አዲስ ቀረቡ

5. አቶ ባይሳ ኡርጋ ቀረቡ 6. አቶ አማኑኤል ይብራህ

7. ወ/ሮ መሰረት ሙላቱ

ተጠሪ፤ የኢትዮጲያ መድሀኒት ፋብሪካ ጠበቃ ኃይሉ ካሳዬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

ጉዳዩ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.294359 ጥቅምት 5 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በሰጠው ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ በሰበር ታይቶ እንዲታረም አመልካቾች ህዳር 11 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን የአመልካቾች ክስ ባጭሩ፤

በተከሳሽ ማህበር በተለያየ ጊዜ በተለያየ የስራ ዘርፍ ተቀጥረው ሲሰሩ መቆየታቸውን እና ጥፋት ፈጽመው የቃልም ሆነ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠበት ሁኔታ ያለመኖሩን ገልጸው ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ሆነን መብታችንን ስለጠየቅን ድርጅቱ ያለአግባብ ከስራ ያሰናበተን ስለሆነ ወደ ስራ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮአረጋጋጫዓለማአየገለግልም!

አንድንመለስ እንዲወሰን ይህ ካልሆነም ስንብቱ ህገወጥ ተብሎ ከህገወጥ ስንብት ጋር ተያያዥ የሆኑ ክፍያዎች ከወጪ እና ኪሳራ ጋር እንዲከፈላቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪም ድርጅቱ የሰው ልጅን ፈዋሽ መድሀኒት አምራች እንደመሆኑ መጠን ከሳሾች ከፍተኛ የስራ ዲሲፕሊን በሚጠይቅ የስራ ድርሻ ተመድበው ሲሰሩ ድርጅቱን ምንም አይነት ፍቃድ ሳይጠይቁ በስራ ሰአት በስራ ቦታ ጊቢ ውስጥ በጩሀት እና በመፈክር የስራ ማቆም አድማ እና ህገወጥ ስብሰባ አድርገው በድርጅቱ ማኔጅመንት ላይ ወከባ በሚፈጥር እና የድርጅቱን መሰረታዊ ስራ በሚያውክ ሁኔታ ስለተገኙ በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27 (1)ረ/ቀ/ሰ እና 14 (2)ሰ እንዲሁም በህብረት ስምምነት አንቀጽ 6(1) መሰረት የስራ ውላቸው በህግ አግባብ የተቋረጠ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ በወቅቱ የተጠሪ ድርጅት 200 የሚሆኑ ሰራተኞች የቦነስ ጥያቄን መነሻ በማድረግ በድርጅቱ ጊቢ ውስጥ በስራ ሰአት የመብት ጥያቄ ማንሳታቸውን እንጂ ስብሰባ ስለማድረጋቸው አልተረጋገጠም፣ ተጠሪ የህብረት ስምምነቱን አንቀጽ 6 (4) ን በማንሳት የሚያቀርበው ክርክር ምንም እንኳን የሰራተኛ ማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ለማድረግም ይሁን አስቸኳይ ስብሰባ ለማድረግ ድርጅቱን ፈቃድ መጠየቅ እንዳለበት የደነገገ ቢሆንም ይህ ስምምነት ተግባራዊ የሚደረገው ለሰራተኛው የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ብቻ እንደሆነ በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ ከመደንገጉም በተጨማሪ አመልካቾች የተባለውን ስብሰባ ስለማድረጋቸው አልተረጋገጠም በማለት የተጠሪን ክርክር ውድቅ አድርጎ ስንብቱ ህገወጥ ነው ስለሆነም ተጠሪ በአዋጁ አንቀጽ 43(2) እና (5) መሰረት ለአመልካቾች የ6 ወር ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራቸው እንዲመልሳቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ አመልካቾች ቦነስን አስመልክቶ ተጠሪ ያሳለፈውን ውሳኔ በመቃወም በድርጅቱ የስራ ቦታ እና የስራ ሰአት በድምጽ ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል በህብረት ስምምነቱ መሰረት አሰሪው ሳይፈቅድ በስራ ሰአት ስብሰባ ማካሄድ ለማንኛውም ሰራተኛ የተከለከለ ነው፤በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ አንቀጽ 14(2)ሰ እና 27(2)ቀ መሰረት ይህ ድርጊት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ስለሆነ አመልካቾች የተጠሪን ፍቃድ ሳያገኙ ስብሰባ በማድረጋቸው ምክንያት ተጠሪ የስራ ውላቸውን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጡ ተገቢ ነው በማለት የአመልካቾችን ክርክር ውድቅ በማድረግ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ዉሳኔ በመሻር ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህንን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ባጭሩ በወቅቱ ህገወጥ ስብሰባ ስለማድረጋችን በተጠሪ ምስክሮችም ቢሆን አልተረጋገጠም የተረጋገጠው የመብት ጥያቄ ማንሳታችን ነው ይህ ደግሞ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አይደለም ስለሆነም የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ አግባብ መርምሮ የሰጠውን ውሳኔ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሻር የሰጠው ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻርልን ይገባል የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት አመልካቾች ተጠሪ የለጠፈውን የቦነስ ክፍያን የተመለከተ ማስታወቂያ በመቃወም ፈጽመዋል የተባለው ድርጊት በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 14(2)ሰ የተሸፈነ እና ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብት የሚችል ድርጊት ስለመሆኑ ተጠሪ ባለበት ለመመርመር ያስችል ዘንድ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ባዘዘው መሰረት ተጠሪ በሰጠው መልስ በወቅቱ አመልካቾች የፈጸሙት ድርጊት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ስንብት የሚያሰጥ ስለሆነ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ዉሳኔ ተገቢ ስለሆነ የተፈጸመበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም የሰበር አቤቱታዉ ተሰርዞ ዉሳኔዉ ሊጸና ይገባል በማለት ጥር 22 ቀን 2015ዓ.ም የተጻፈ የመልስ ክርክሩን አቅርቧል፡፡ አመልካችቾም የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት በተለያየ የስራ ዘርፍ ተቀጥረው ሲሰሩ መቆየታቸውን እና ጥፋት ፈጽመው የቃልም ሆነ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠበት ሁኔታ ያለመኖሩን ገልጸው ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ሆነን መብታችንን ስለጠየቅን ድርጅቱ ያለአግባብ ከስራ ያሰናበተን ስለሆነ ወደ ስራ አንድንመለስ እንዲወሰን ይህ ካልሆነም ስንብቱ ህገወጥ ተብሎ ከህገወጥ ስንብት ጋር ተያያዥ የሆኑ ክፍያዎች ከወጪ እና ኪሳራ ጋር እንዲከፈላቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪም ድርጅቱ የሰው ልጅን ፈዋሽ መድሀኒት አምራች እንደመሆኑ መጠን ከሳሾች ከፍተኛ የስራ ዲሲፕሊን በሚጠይቅ የስራ ድርሻ ተመድበው ሲሰሩ ድርጅቱን ምንም አይነት ፍቃድ ሳይጠይቁ በስራ ሰአት በስራ ቦታ ጊቢ ውስጥ በጩሀት እና በመፈክር የስራ ማቆም አድማ እና ህገወጥ ስብሰባ አድርገው በድርጅቱ ማኔጅመንት ላይ ወከባ በሚፈጥር እና የድርጅቱን መሰረታዊ ስራ በሚያውክ ሁኔታ ስለተገኙ በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 14 (2)ሰ እና 27 (1) /ቀ/ እንዲሁም በህብረት ስምምነት አንቀጽ 6(1) መሰረት  ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮአረጸጸምዓለማአ የገለግልም!

በመሰረቱ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 14(2) ለ መሰረት በህብረት ስምምነት ከተፈቀደው ውጪ ወይም አሰሪው ሳይፈቅድ በስራ ሰአት ስብሰባ ማድረግ በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) (ቀ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት እንደሆነ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ከዚህ አንጻር አሁን የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ተጠሪ የአመልካቾችን የስራ ውል ያቋረጠው አመልካቾች ከአሰሪው ፍቃድ ውጪ በስራ ሰአት ስብሰባ አካሂደዋል በሚል ሲሆን የአመልካቾች ክርክር ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ሆነን መብታችንን ስለጠየቅን ድርጅቱ ያለአግባብ ከስራ አሰናበተን እንጂ ያደረግነው ስብሰባ የለም የሚል ነው፡፡

የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካቾች በወቅቱ ስበሰባ አድርገዋል አላደረጉም የሚል ጭብጥ በመያዝ ምንም እንኳን የህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 6 (4) የሰራተኛ ማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ለማድረግም ይሁን አስቸኳይ ስብሰባ ለማድረግ ድርጅቱን ፈቃድ መጠየቅ እንዳለበት የደነገገ ቢሆንም ይህ ስምምነት ተግባራዊ የሚደረገው ለሰራተኛው የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ብቻ እንደሆነ በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ ከመደንገጉም በተጨማሪ አመልካቾች በወቅቱ ከሌሎች የድርጅቱ ሰራተኞች ጋር በመሆን የመብት ጥያቄ ከማንሳታቸው በስተቀር አንድ ስብሰባ ሊያሟላ የሚገባውን መስፈርት ባሟላ መልኩ የተባለውን ህገወጥ ስብሰባ ስለማድረጋቸው አልተረጋገጠም ስለሆነም ተጠሪ የአመልካቾችን ስራ ውል ያቋረጠው ያለአግባብ ነው በማለት አትቶ አመልካቾች የ6 ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ድርጅቱ በነስን አስመልክቶ ያሳለፈውን ውሳኔ በመቃወም በድምጽ ጥያቄ በማቅረብ ህገወጥ ስብሰባ ማድረጋቸው ተረጋግጧል በማለት አትቶ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ውሳኔ የሰጠው፡፡

በመሰረቱ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ለመሻር ለውሳኔያቸው ህጋዊ እና በቂ ምክንያት መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1) እና ይህንኑ ድንጋጌ ጠቅሶ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 38844 እና መ.ቁ. 58540 ላይ የሰጣቸዉ አስገዳጅ ዉሳኔዎች ያስገነዝባሉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ሲወስን አመልካቾች በድምጽ ጥያቄ በማቅረብ ህገወጥ ስብሰባ ማድረጋቸው ተረጋግጧል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍ/ዮ አ ረ ጸ ጸ ምዓለ ማአ የገ ለግልም!

ከማለት በስተቀር የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀረቡት የግራ ቀኝ ምስክሮች አመልካቾች የመብት ጥያቄ ከማቅረባቸው በስተቀር በወቅቱ ስብሰባ ስለማድረጋቸው አልተረጋገጠም በማለት የሰጠውን ውሳኔ ለመሻር የሚያስችል በወቅቱ አመልካቾች ስብሰባ ስለማድረጋቸው አስረጂ የሆነ በቂ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ አልገለጸም፡፡

በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቂ ምክንያት ሳይኖር እና ሳይገልጽ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የአሁን ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ዉል በመቋረጥ ያሰናበታቸዉ በሕግ አግባብ ነዉ ደመወዝ ሊከፈላቸዉ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የአዋጁን ድንጋጌዎች ያልተከተለ ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ያሰናበታቸዉ በሕግ አግባብ ነዉ በማለት የ6 ወር ደመወዝ ለአመልካቾች ሊከፈላቸዉ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.294359 በ5/2/2016 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.132854 መጋቢት 8 ቀን 2015ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43 (5) እና ይህንን ድንጋጌ የሚተረጎምበትን አግባብ በማመልከት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21730 እና በሌሎችም ተመሳሳይ መዝገቦች ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት አመልካቾች ወደ ስራ እንዲመለሱ በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ የጸና ስለሆነ ከ1 አመት የማይበልጥ ደመወዝ ሊከፈላቸው ስለሚገባ እና አመልካቾች አሰቀድሞ በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የ6 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የተወሰነላቸው ስለሆነ በተጨማሪ የ6 ወር ደመወዝ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍ ሮ ዮ አ ረ ጸ ጸ ምዓ ለ ማአ የ ገ ለ ግል ም!

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አይገለግልም!